ዜና
አመዝኤ



## በዚህ ዕትም ውስጥ

አመዝኤና "አንድ ብር ለአንድ ወገን" የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ከ8.2 ሚሊዮን ብር በላይ ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች ማቋቋሚያ እንዲውል ወሰኑ::
ገጽ 3

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከብር 55 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል::
ገጽ 4

በጎርፍ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች የመልሶ ማቋቋም ተግባራት ተጠናክረው እየተካሄዱ መሆኑ ተገለፀ::
ገጽ 5

በሰኔ ወር ከ26 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሠራጭቷል::
ገጽ 6

የአመዝኤ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሩዋንዳ መንግሥት ባለሥልጣናትን ተቀብለው አነጋገሩ::
ገጽ 7

የበልግ አዝመራንና የአርብቶ አደር አካባቢ ሁኔታዎችን የሚያጠኑ ቡድኖች ተሰማሩ::
ገጽ 7

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት
ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት
የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et



# የክረምቱ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ መምጣቱ የጎርፍ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ተመለከተ

በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የበልጉ ዝናብ ሳያቋረጥ ከክረምቱ ዝናብ አጀማመር ጋር መገጣጠሙና በሰኔ ወር በአብዛኛው የአገራችን ክፍሎች የክረምቱ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመምጣቱ የቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት የጎርፍ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ተገለፀ::

የአመዝኤ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት ብሔራዊ ሜቲዮሮሎጂ ኤጀንሲ የክረምቱ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንበያን ጠቅሶ እንዳስታወሰው በቅርቡ በአጠቃላይ በአብዛኛው የአገራችን ክፍሎች የክረምቱ ዝናብ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የመሆን ዕድሉ ከ70-80% ይሆናል:: በተለይም በምዕራብ ትግራይ ፣ ምዕራብና መካከለኛው አማራ ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ ጋምቤላ ፣ ምዕራብና መካከለኛው ኦሮሚያ ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች



ሰሜናዊ ክፍል መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪም ለክረምቱ ዝናብ መኖርና መጠንከር እገዛ የሚያደርጉ የአየር ሁኔታ ገፅታዎች በሚጠናከሩበት ጊዜ በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ነጎድጓድ አዘልና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል በተለምዶ በጎርፍ በሚጠቁ ዝቅተኛ አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት የመኖር አጋጣሚ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት ማሳደሩንም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት አመልክቷል::

ክረምቱ ከመግባቱ በፊት የነበረው የበልግ ዝናብ በዋናነት የበልግ ተጠቃሚ የሆኑ የምሥራቃዊ ትግራይና አማራ ፣ አብዛኛው አፋር እንዲሁም አብዛኛው ደቡባዊ የሶማሌ ክልልና ጋምቤላ ምዕራባዊ ጫፍ ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ ያስመዘገቡ ቢሆንም ቀሪዎቹ አብዛኞዎቹ የአገራችን ክፍሎች መደበኛ የሆነ ዝናብ ማግኘታቸውን ሪፖርቱ ጠቁሞ በተለይም በሚያዝያና በግንቦት 1999 ዓ.ም የነበረው ዝናብ በመጠንም በሥርጭትም የተጠናከረና የተስፋፋ መሆኑንና በአንዳንድ ቦታዎችም ለተከታታይ ቀናት ከባድ ዝናብና አልፎ አልፎም ቅፅበታዊ ጎርፍ የተከሰተበት ሁኔታ መፈጠሩን ገልጿል:: በመሆኑም በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የበልጉ ዝናብ ሳይቋረጥ ከክረምቱ ዝናብ አጀማመር ጋር መገጣጠሙና በሰኔ ወር በአብዛኛው የአገራችን ክፍሎች የክረምቱ ዝናብ አጀማመር ጋር ተዳምሮ የአፈሩን

ውሃ የመሸከም አቅም ወትሮ ከተለመደው ጊዜ አስቀድሞ እንዲቀንስ ዋንኛ ምክንያት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጎርፍ አደጋ ስጋቱን ይበልጥ እንዳባባሰው ሪፖርቱ አብራርቷል፡፡

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ ከተለያዩ የአገራችን ከፍተኛ ቦታዎች እየተነሱ በዝቅተኛ ተፋሰስ አካባቢዎች ቅፅበታዊ የጎርፍ አደጋ የሚያስከትሉትና ጉዳቱ ጎልቶ የሚታይባቸው ቦታዎች በጣም በርካታ ናቸው፡፡

ባለፈው ዓመት የመጀመሪያው የጎርፍ አደጋ ሪፖርት ከኦሮሚያ ክልል የደረሰው ሐምሌ 24/1998 ዓ.ም ከምዕራብ ሸዋ ዞን ከኤጀሬ ፣ ሰበታ አዋሶ እና ኢሉ ወረዳዎች እንደነበር ያስታወሰው ይኸው ሪፖርት የዘንድሮው ክረምት ዝናብ አስቀድሞ በመጀመሩ በሰኔ ወር ውስጥ የተለያዩ የጎርፍ አደጋዎች ክስተት ከደቡብ ኦሞ ዞን ጅንካ፣ ከወላይታ ዞን ሁምቦና በተለያዩ አካባቢዎች መድረሱ ሲታይ ቀጣዮቹን ወራት ሐምሌን ነሐሴንና መስከረምን እጅግ አሳሳቢ እንደሚያደርጋቸው አስታውቋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከሚታየው ከፍተኛ የሆነ የክረምወቅት አጀማመር የቀጣዩ ወራት ትንበያ ትክክለኛነት ከ70% በላይ የመሆን ዕድል ፣ ከዚህ በተጨማሪም ባለፈው በልግ ወቅትም በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች የነበረው ዝናብ መደበኛ ፈሩን የተከተለና በአንዳንድ አካባቢዎች የክረምቱ ዝናብ እስኪጀምር ድረስ የቀጠለ በመሆኑ የአፈሩን ውሃ የመሸከም አቅም በመቀነስ ከአሁን በኋላ የሚዘንበው ዝናብ በቀላሉ ወደ ጎርፍነት ሊቀየር እንደሚችል ያመለከተው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት ይህም ቅፅበታዊ የጎርፍ አደጋ መንስኤ ሊሆንና ዋና ዋና ግድቦችም ከወትሮው ጊዜ ቀደም ብለው ሊሞሉ ይችላሉ የሚል ስጋት አሳድሯል፡፡

ከዚህ አኳያ በአሁኑ ጊዜ በብሔራዊ ሜትዮሮሎጂ ኤጀንሲ ከተሰጠው ትንበያ አንፃር መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚዘንብባቸው ከተጠቆሙት አካባቢዎች በተጨማሪ በዝቅተኛው ምሥራቃዊ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ አካባቢዎች ጭምር ለጎርፍ አደጋ የሚጋለጡበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል ሪፖርቱ አስታውቋል፡፡

ሪፖርቱ አያይዞም ከዚህ እውነታ በመነሳት ለጎርፍ ተጋላጭ የሆነው ህብረተሰብና በየደረጃው የሚገኙ የመስተዳድር አካላትና ችግሩ የሚመለከታቸው ከወዲሁ የበኩላቸውን ጥንቃቄ ካላደረጉ በሚቀጥሉት ወራት ሊደርስ የሚችለው አደጋ ከአለፈውም ዓመት የከፋ ሊሆን እንደሚችል አመልክቷል፡፡

በመሆኑም ባለፉት ዓመታት ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የነበሩ አካባቢዎች በሙሉ የሁኔታውን አሳሳቢነት ተገንዝበው በየደረጃው የሚገኙ የመስተዳድር አካላትና ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ተባባሪ ወገኖች ከወዲሁ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ እንዲያደርጉና የብሔራዊ ሜቲዮሮሎጂ ኤጀንሲና አመዝኤ የሚሠጧቸውን መግለጫዎችና ማስጠንቀቂያዎች በየጊዜው በቅርብ ትኩረት ሰጥተው ሊከታተሉት እንደሚገባ አሳስቧል፡፡

ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘው ሕብረተሰብም ከወዲሁ የሚታየውን አሳሳቢ ሁኔታ በመገንዘብ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አመዝኤ በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ ይወዳል፡፡

በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የበልጉ ዝናብ ሳያቋረጥ ከክረምቱ ዝናብ አጀማመር ጋር መገጣጠሙና በሰኔ ወር በአብዛኛው የአገራችን ክፍሎች የክረምቱ ዝናብ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመምጣቱ የቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት የጎርፍ አደጋ ሊከሰት ይችላል የሚለ ስጋት አለ፡፡

አመዝኤ

ለጎርፍ ተጋላጭ የሆነው ህብረተሰብና በየደረጃው የሚገኙ የመስተዳድር አካላትና ችግሩ የሚመለከታቸው ከወዲሁ የበኩላቸውን ጥንቃቄ ካላደረጉ በሚቀጥሉት ወራት ሊደርስ የሚችለው አደጋ ከአለፈውም ዓመት የከፋ ሊሆን እንደሚችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርቱ አመልክቷል፡፡

# አመዝኤና “አንድ ብር ለአንድ ወገን” የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ከ8.2 ሚሊዮን ብር በላይ ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች ማቋቋሚያ እንዲውል ወሰኑ

የአንድ ብር ለአንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ በ1994/95 ዓ.ም በሀገራችን ተከስቶ በነበረው አስከፊ የድርቅ አደጋ ሳቢያ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመታደግ ያሰባሰበውን ከ 8.2 ሚሊዮን ብር በላይ በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ እንዲውል መወሰኑን አስታወቀ::



በወቅቱ ተከስቶ የነበረውን አስከፊ የድርቅ አደጋ ለመከላከል ከመንግሥት፣ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከተባባሪ ወገኖች ጎን በመሰለፍ ባካሄደው የዕርዳታ አሰባሰብ እንቅስቃሴ ወቅት በእህልና በቁሳቁስ አሰባስቦት የነበረው ዕርዳታ በወቅቱ ሥራ ላይ መዋሉን ኮሚቴው አስታውሶ በጥሬ ገንዘብ ተሰብስቦ የነበረውና ለዚሁ ዓላማ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ የተቀመጠውን ብር 8,267,391.56 /ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከ56 ሳንቲም/ ለድሬዳዋ ፣ ለደቡብ ብሐር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ፣ ለአማራና ለሶማሌ ክልሎች የጎርፍ ተጎጂ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ እንደየአደጋው ጉዳትና መጠን ተሰልቶ እንዲከፋፈል ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ /አመዝኤ/ ጋር በተደረገው ውይይት ከስምምነትና ውሳኔ ላይ ደርሷል::

የፌዴራል አመዝኤና ኮሚቴው ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በአመዝኤ የስብሰባ አዳራሽ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻለ አንድ ብር ለአንድ ወገን በተሰኘ መርህ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ አርአያነት ባለው የዕርዳታ ማሰባሰብ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ በወቅቱ የተሰበሰበው ገንዘብ ከዕለት ደራሽ ዕርዳታ ይልቅ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሀገሪቱ ለምታደርገው ጥረት አጋዥ በሚሆኑ ተግባራት ላይ ቢውል በተጠቃሚዎቹ ሕይወት ላይ ዘላቂና ተጨባጭ ውጤት በማስመዝገብ ድጋፍ ላበረከቱ ወገኖችም የህሊና እርካታ እንደሚያስገኝ በማመን ለዚሁ ተግባር እንዲውል ተስማምተው እንደነበረ አስታውሰዋል::

በዚሁ ስምምነት መሠረት አመዝኤና ኮሚቴው ገንዘቡ በዘላቂነት የተጠቃሚዎችን ሕይወት በሚለውጥና የምግብ ዋስትናን በሚደግፍ ሥራ ላይ የሚውልበትን ግልፅ አቅጣጫ አስቀምጠው ወደተግባር ለመሸጋገር በተደረገው እንቅስቃሴ በወቅቱ በድርቁ ሳቢያ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው አራት ክልሎች ፕሮጀክቶች እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም ከተወሰኑ ክልሎች የቀረቡት የፕሮጀክት ረቂቆች በሁለቱም ወገኖች በተሰየሙ ባለሙያዎች



የአንድ ብር ለአንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ በ1994/95 ዓ.ም በሀገራችን ተከስቶ በነበረው አስከፊ የድርቅ አደጋ ሳቢያ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመታደግ ያሰባሰበውን ከ 8.2 ሚሊዮን ብር በላይ ለድሬዳዋ ፣ ለደቡብ ብሐር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ፣ ለአማራና ለሶማሌ ክልሎች የጎርፍ ተጎጂ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ እንደየአደጋው ጉዳትና መጠን ተሰልቶ እንዲከፋፈል ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ /አመዝኤ/ ጋር በተደረገው ውይይት ከስምምነትና ውሳኔ ላይ ደርሷል::

የአንድ ብር ላንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወ/ሪት ሰሎሜ ታደሰ እንደገለጹት መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፣ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የመንግሥት ፣ የግል ተቋማትና ግለሰቦች የአንድ ብር ለአንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሰብ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ ያበረከቱት ድጋፍና ያሳዩት ጥልቅ የወገን ፍቅር ምንጊዜም ከህሊና የማይጠፉ ክብርና ሞገስ የሚቸረው አኩሪ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

ተገምግመው የሚጠበቀውን ደረጃ ባለማሟላታቸውና ተፈፃሚነታቸውም አስተማማኝ ባለመሆኑ አወዳድሮ በመምረጥ ሥራ ላይ ለማዋል ባለመቻሉና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች ገንዘቡ በጥቅም ላይ ሳይውል ቆይቷል፡፡ ሆኖም ከዚህ በላይ ጥቅም ላይ ሳይውል ማቆየቱ ተገቢ ባለመሆኑና በአሁኑ ወቅትም በተፈጥሮ አደጋ ሳቢያ የተፈናቀሉ ወገኖች በመኖራቸውና ለተመሳሳይ ወቅታዊ የሰብዓዊ ዕርዳታ ማዋሉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ለጎርፍ ተጎጂዎች መልሶ ማቋቋሚያ እንዲውል መመደቡን አስታውቀዋል፡፡

የአንድ ብር ላንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወ/ሪት ሰሎሜ ታደሰ እንደገለጹት መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፣ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የመንግሥት ፣ የግል ተቋማትና ግለሰቦች የአንድ ብር ለአንድ ወገን የዕርዳታ አሰባሰብ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ ያበረከቱት ድጋፍና ያሳዩት ጥልቅ የወገን ፍቅር ምንጊዜም ከህሊና የማይጠፉ ክብርና ሞገስ የሚቸረው አኩሪ ተግባር ነው ብለዋል፡፡ አያይዘውም በወቅቱ ያበረከቱት የምግብና የቁሳቁስ ድጋፍ በሥራ ላይ መዋሉና የለገሱትም ገንዘብ በተፈጥሮ አደጋ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን ለማቋቋም ተግባር እንዲውል መደረጉም ይህንን እውነታ ያገናዘበ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

ይህም ውሳኔ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ትላንትም ፣ ዛሬም አደጋ በተከሰተ ወቅት ሁሉ ከዕለት ጉርሱ ፣ ከዓመት ልብሱ ቀንሶ ተጎጂ ወገኖቹን ሲታደግ ለቆየው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ የህሊና እርካታ እንደሚሰጥ በማመን ፣ አመዝኤና ኮሚቴው ሕዝቡ ላበረከተው አስተዋጽዖ በተጎጂ ወገኖች ስም ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

## በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከብር 55 ሚሊዮን በላይ ተለግሷል፡፡

◆ **ብር 53 ሚሊዮን ለክልሎች ተመድቧል**

ባለፈው ዓመት ክረምት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በደረሱ የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ከአደጋዎቹ ክስተት ማግስት ጀምሮ ከሀገር ውስጥና ከውጭ



ዕርዳታ ለማሰባሰብ በተደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እስከ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ከብር 55 ሚሊዮን በላይ ለማሰባሰብ መቻሉ ታውቋል፡፡

ይኸው የገንዘብ መጠን ሊሰበሰብ የቻለው በሀገር ውስጥ የተለያዩ የህበረተሰቡ ክፍሎች ፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሠራተኞቻቸው፣ የግል ድርጅቶች ፣ የሀይማኖት ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት እንደሁም ከሀገር ውጭ በውጭ

ባለፈው ዓመት ክረምት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በደረሱ የጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ከአደጋዎቹ ክስተት ማግስት ጀምሮ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በተደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እስከ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ከብር 55 ሚሊዮን በላይ ለማሰባሰብ መቻሉ ታውቋል።

ዜና

ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ባደረጉት ልገሳና የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው ባቋቋማቸው የተለያዩ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴዎች አማካይነት በተደረጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት የተገኘው ዕርዳታ የአውሮጠ ህብረት ለጎርፍ ተጎጂዎች ለመለገሥ ቃል የገባውን ብር 70 ሚሊዮን ፣ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በኩል የተሰበሰበውን እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከውጭ በዓይነት የተለገሡ ዕርዳታዎችን አይጨምርም።

ይኸ በዚህ እንዳለም የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም ከተሰባሰበው ገንዘብ ውስጥ ከብር 53 ሚሊዮን በላይ በሁለት ዙሮች እንደደረሰው አደጋ መጠ ንና ቅድሚያ በሚሰጣቸው የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ጥናት መሠረት እየተሰላ ለክልሎች ተመድቧል።

በዚሁ መሠረት በሁለት ዙሮች በተደረገው ድልድል ለድሬዳዋ ብር 24 ሚሊዮን 685 ሺህ ፣ ለደቡብ ህዝቦች ብር 17 ሚሊዮን 378 ሺህ ፣ ለአማራ ብር 5 ሚሊዮን 516 ሺህ እና ለሱማሌ ብር 5 ሚሊዮን 422 ሺህ የተመደበ መሆኑ ታውቋል።

ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ብር ለአንድ ወገን ዕርዳታ አሰባሳቢ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ አሰባስቦት የነበረው ብር 8 ሚሊዮን በጎርፍ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ እንዲውል በዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴውና በአመዝኤ መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት ይኸው ገንዘብ በጥናት ላይ በተመሠረተ የፍላጎት ስሌት በ3ኛ ዙር ለየክልሎቹ የተመደበ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል።

## በጎርፍ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች የመልሶ ማቋቋም ተግባራት ተጠናክረው እየተካሄዱ መሆኑ ተገለፀ

ባለፈው ዓመት ክረምት በተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች በደቡብ ኦሞ ዞን ፣ በድሬዳዋ ፣ በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን ፣ በጋምቤላ ክልል እና በአፋር ክልል በተወሰኑ ወረዳዎች ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም የሚከናወኑ ተግባራት በተጠናከረ መልኩ እየተካሄዱ መሆኑ ተገልጿል።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ሰኔ 14 ቀን 1999 ዓ.ም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበው የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው ባለፈው 1998 ዓ.ም ክረምት ወራት በተለይም ሐምሌ መጨረሻና ነሐሴ መጀመሪያ ላይ ድሬዳዋን ጨምሮ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን ፣ በአፋር ክልል ዞን 1 እና 2 ፣ በጋምቤላ ክልል ኑዌር ፣ኢታንግ እና አኝዋክ ዞኖች ከዛም በኋላ በጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም በሱማሌ ክልል ጎዴ ፣አፍዴር እና ቆራሔ ዞኖች በሚገኙ 28 አርብቶ አደር ወረዳዎች በደረሱ ድንገተኛ ደራሽ ጎርፍ እና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋዎች ሳቢያ ከ456 ሺህ በላይ ህዝብ ጉዳት ደርሶበታል። ከዚህም ውስጥ 174 ሺህ 960 ህዝብ ከቤት ንብረቱ በመፈናቀሉ ሳቢያ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ፈላጊ ሆኖ ነበር።

ከዚሁ አንፃር ኤጀንሲው ካለበት ተግባርና ኃላፊነት አኳያ በወቅቱ ከሌሎች የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት አደጋው በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ከማድረጉም በላይ ለአደጋው ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች የዕለት ዕርዳታ እና ቁሳቁስ እንዲሁም

> ባለፈው ዓመት ክረምት በተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች በደቡብ ኦሞ ዞን ፣ በድሬዳዋ ፣ በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን ፣ በጋምቤላ ክልል እና በአፋር ክልል በተወሰኑ ወረዳዎች ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም የሚከናወኑ ተግባራት በተጠናከረ መልኩ እየተካሄዱ መሆኑ ተገልጿል።

ጊዜያዊ መጠለያ በማቅረብ ረገድ ጉልህ ተግባራትን ማከናወኑን የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻል ለኮሚቴው ባቀረቡት ሪፖርት አመልክተዋል።

በቀጣይ ጊዜያትም ኤጀንሲው የዕለት ዕርዳታዎችን ከማቅረብ ባሻገር በአደጋው ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል ዕርዳታ ከሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ለማሰባሰብ ከብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴውና በሥሩ ከተቋቋሙት ንዑሳን ኮሚቴዎች ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርግ መቆየቱ በሪፖርቱ ተጠቅሷል።

በዚህም የዕርዳታ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል በኩል የተሰበሰበውንና በዓይነት የተለገሠውን ሳይጨምር እስከ ሰኔ ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ከብር 55 ሚሊዮን በላይ ለማሰባሰብ መቻሉም ታውቋል።

በድሬዳዋ እና በአርብቶ አደር አካባቢዎቹ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ያለው የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናቶች ከተካሄዱ በኋላ የየአካባቢዎቹ ፍላጎት ተለይቶ የተሰበሰበው ዕርዳታ ፍላጎቱን መሠረት በማድረግ ተሰልቶ ለየአካባቢዎቹ መደልደሉንም ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በፌዴራል ደረጃ ከሚደረገው የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴ በተጨማሪ ክልሎችም በየራሳቸው በኩል ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ እንደመሆኑ መጠን በፌዴራል እና በክልሎች ደረጃ የሚደረግ የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴ ለማጣጣም በየጊዜው ምክክር እንደሚደረግ ለመረዳት ተችሏል።

## በሰኔ ወር ከ26 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሠራጭቷል

በተለያዩ ክልሎች በሠው ሠራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በሰኔ ወር በጠቅላላው 26 ሺህ 640.50 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ የተሠራጨ



መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የምግብ ዕርዳታው የተሠራጨው በአምስት ክልሎች ውስጥ ለሚገኙ 21 ወረዳዎችና ለድሬዳዋ አስተዳደር የጎርፍ ተጎጂዎች ሲሆንዓይነቱም እህል ፣ የምግብ ዘይት፣ ጥራጥሬ እና አልሚ ምግብን ያካተተ እንደሆነም ለመረዳት ተችሏል።

ለየክልሎቹ የሚላከው የምግብ ዕርዳታ በየክልሎቹ እንደተከሰተው አደጋ ዓይነትና

መጠን እንዲሁም የተጎጂ ህዝብ ብዛት የሚለያይ ነው። በዚህም መሠረት በሰኔ ወር ከተሠራጨው 26 ሺህ 640.50 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 12 ሺህ 919.50 ኩንታል ለኦሮሚያ ፣ 7 ሺህ 878 ኩንታል ለደቡብ ህዝቦች ፣ 1 ሺህ 687 ኩንታል ለድሬዳዋ ፣ 1 ሺህ 451 ኩንታል ለአፋር 1 ሺህ368 ኩንታል ለአማራ እና 1 ሺህ 337 ኩንታል ለትግራይ የተላከ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## የአመዝኤ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሩዋንዳ መንግሥት ባለሥልጣናትን ተቀብለው አነጋገሩ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገብረመድህን በላይ በኢትዮጵያ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የመጡትን የሩዋንዳ መንግሥት ባለሥልጣናት ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተቀብለው አነጋገሩ።



ባለፈው ዓመት ክረምት በተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች በደቡብ ኦሞ ዞን ፣ በድሬዳዋ ፣ በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን ፣ በጋምቤላ ክልል እና በአፋር ክልል በተወሰኑ ወረዳዎች ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም የሚከናወኑ ተግባራት በተጠናከረ መልኩ እየተካሄዱ መሆኑ ተገልጿል።



ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ የኢኮኖሚያዊ ዕቅድ ኃላፊ ሚስስ ሞኒክ ንሶንዛጋንዋና በሚኒስትር ዲኤታ ማዕረግ የማህበረሰብ ልማትና ማህበራዊ ጉዳዮች ኃላፊ ሚስ ክስቲን ንያኒን ተቀብለው ባነጋገሩበት ጊዜ ስለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አመሠራረት ፣ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም ወቅታዊ የአደጋ መከላከል ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ገለፃ አድርገውላቸዋል።

ባለሥልጣናቱም የአደጋ ሁኔዎችን በይፋ በማሳወቅ ረገድ ኤጀንሲው የሚከተለውን የግልፅነት አሠራርና ሰብዓዊ ዕርዳ በወቅቱ ከማድረስ አኳያ ያለውን ልምድ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ላቀረቡት ጥያቄ ዋና ዳይሬክተሩና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል።

አደጋን በመከላከል ረገድ በሩዋንዳ ያለውን ሁኔታ ያብራሩት ባለሥልጣናቱ በልምድ ልውውጡና በተደረገላቸው ገለፃ መደሰታቸውን ገልፀዋል።

## የበልግ አዝመራንና የአርብቶ አደር አካባቢ ሁኔታዎችን የሚያጠኑ ቡድኖች ተሰማሩ

የበልግ ወቅትን የሰብል አምራችና የአርብቶ አደር አካባቢ ሁኔታዎችን የሚያጠኑ 16 አጥኚ ቡድኖች ከሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሰማሩ።

ለሁለት ሳምንታት የሚካሄደው ይኸው ጥናት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በስተቀር ሁሉንም

ክልሎች የሚሸፍን ሲሆን ፣ የበልግ አዝመራ ፣ የእንስሳት ፣ የውሀና የግጦሽ ፣ የገበያና የጤና ሁኔታዎችን እንዲሁም ችግሮችን ለመቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎችን ይዳስሳል፡፡

የበልግ ወቅትን የሰብል አምራችና የአርብቶ አደር አካባቢ ሁኔታዎችን የሚያጠኑ 16 አጥኚ ቡድኖች ከሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሰማርተዋል፡፡

የዘንድሮውን ጥናት ከሌሎቹ ጊዜያት ለየት የሚያደርገው በትግራይ ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም በሶማሌ ክልሎች የሰዎችን የኑሮ መሠረት መነሻ ያደረጉ በቤተሰብ የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ያተኮረ አዲስ የአጠናን ስልት ተቀይሶ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የአጠናን ስልት አደጋው ከመድረሱ በፊት የሰዎች ጥሪት ሳይሟጠጥ አስቀድሞ ተገቢውን ዝግጅት በማሟላት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ የተሻለ ስልት መሆኑ ከመታመኑም በላይ የዕርዳታ ፈላጊዎችን ብዛት በትክክል በመለየትና ፍላጎትን በመተመን ረገድ ይበልጥ አስተማማኝነት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ ይኸው የአጠናን ስልት በሂደት እየጎለበተና እየተሻሻለ ሲመጣም ተጎጂዎችን በነፍስ ወከፍ ለመለየት በእርግጥም መረዳት የሚገባቸው ወገኖች ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችልና ያለውን አነስተኛ የዕርዳታ ሀብትም ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ በማዋል የተረጂነት ስሜትን በመቅረፍ ረገድ ሁነኛ ድርሻ እንደሚኖረው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጥናት ላይ ተሳታፊ ለሚሆኑ ባለሙያዎችም ስልጠና መሰጠቱ ታውቋል፡፡

በቀሪዎቹ ክልሎች ግን በሂደት ይህ የአጠናን ስልት ሥራ ላይ እስኪውል ድረስ ለዚህ ዓመት ቀደም ሲል ሲሠራበት የነበረው የአጠናን ስልት እንደሚተገበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

በጥናቱ ላይ ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ 15 ፣ ከብሔራዊ ሚትዮሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት አምስት ፣ ከተ.መ.ድ የተለያዩ አካላት 17 ፣ ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ሁለት ፣ ከተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የህይማኖት ተቋማት 27 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡